# 5ኛ ክፍል

# የሙዚቃ ሲለበስ

## ክፍለ ትምህርት አንድ የሙዚቃ መገለጫዎቹና ጠቀሜታ *(7 ክፍለ ጊዜ )*

***አጠቃላይ ዓላማ፡-*** ተማሪዎች ይህንን ክፍለ ትምህርት ከተማሩ በኋላ፣

- *የሙዚቃን መገለጫዎችና ጠቀሜታን ያውቃሉ፣*

| *ዝርዝር ዓላማዎች* | *ይዘ ት* | *የመማር ማስተማር ዘዴዎች* |
|---|---|---|
| *ተማሪዎች ይህንን ንዑስ ክፍለ ትምህርት ከተማሩ በኋላ፡-*<br>• የሙዚቃን ትጉም ይገልፃሉ።<br>• የሙዚቃ ጥዑመ ለዛ መገለጫዎችን ይዘረዝራሉ።<br>• የሙዚቃ መገለጫዎችን በተለያየ መንገድ በተግባር ያሳያሉ።<br>• ሙዚቃን የሚገልፅ መዝሙር ይዘምራሉ።<br>• መዝሙሩ የሚያስተላልፋቸውን መልእክት ያስረዳሉ። | 1. ***ንዑስ ክፍለ ትምህርት አንድ*** *(3 ክፍለ ጊዜ )*<br>1.1 ሙዚቃ ምንድነው?<br>1.2 ድምፅ (Sound)<br>1.3 የሙዚቃ ጥዑመ ለዛ (ዳይናሚክስ) መገለጫዎች<br>• ፒያኖ<br>• ፎርቴ<br>1.4 ሙዚቃ( 2 ክፍለ ጊዜ) | • ተማሪዎች በራሳቸው ልምድና ተሞክሮ ስለ ሙዚቃ ምንነት ላይ በቡድን እንዲወያዩ ማድረግና የደረሱበትን ፍሬ ሐሳብ በቡድን መሪያቸው አማካይነት ለክፍላቸው ተማሪዎች ተራ በተራ እንዲገልፁ በማድረግ ማበርታታት፣<br>• የተማሪዎችን ሐሳብ መነሻ በመድረግ ስለ ሙዚቃ ምንነት ማብራራት፣<br>• ተማሪዎች በቡድን ተከፋፍለው ስለ ሙዚቃ ድምፅ አፈጣጠር፣ የሙዚቃ ጥዑመ ለዛ መገለጫዎች ስለፒያና ፎርቴ ንድፈ ሐሶቦች ላይ እንዲወያዩና በተግባር እንዲሞክሩ ምሳሌዎችን በመስጠት፣<br>• የድምፅ አፈጣጠርን፣ የፒያኖና ፎርቴ አጠቃቀምን ማሳየት፣<br>• ተማሪዎች ከመምህራቸው ያዩትን ተጨባጭ የተግባር ሙከራዎችን ራሳቸው ደግመው እንዲሠሩ ማድረግ፣<br>• ከፒያኖና ፎርቴ ጋር የተያያዙ ቀላል መልመጃዎችን መስጠት፣<br>• ተማሪዎችን በድምፅ ምድባቸው በመለየት በሙዚቃ ጥዑመ ለዛ ተጠቅመው መዝሙሮችን እንዲለማመዱ ማድረግ፣ |
| • የሙዚቃ ጠቀሜታ ያብራራሉ፣ | **ንዑስ ክፍለ ትምህርት ሁለት** *(2 ክፍለ ጊዜ )*<br>1.5 ሙዚቃና ጠቀሜታው | • ሙዚቃ ለማሕበረሰቡ የሚሰጠውን ጠቀሜታዎች እንዲዘረዝሩ እድል መስጠት፣<br>• ሙዚቃ ለማሕበረሰቡ የሚሰጠውን ጠቀሜታዎች በዝርዝር ማስረዳት ለምሳሌ በሠርግ፣ በበዓላት፣ በልማትና በትምህርት ወዘተ… |

## ክትትልና ግምገማ

- ስለ ሙዚቃ ምንነት ጥያቄ ማቅረብ
- ተማሪዎች የሙዚቃ ጥዑመ ለዛ መገለጫዎችን በንድፈ ሐሳብና በተግባር ማሳየታቸውን ማረጋገጥ፣
- ሙዚቃ ለማሕበረሰቡ የሚሰጠውን ጠቀሜታ እንዲዘረዝሩ በማድረግ ማረጋገጥ፣

**የማስተማሪያ መሣሪያዎች**

- ቴፕሪኮርደር ካሴት ነዛሪ ላስቲኮች ለትምህርቱ ይዘት የሚዘጋጁ ቻርቶች

**ክፍል ትምህርት ሁለት፡- የሙዚቃ ቲዮሪ (18 ክፍለ ጊዜ )**

**አጠቃላይ ዓላማዎች፡-** ይህንን ክፍለ ትምህርት ከተማሩ በኋላ ተማሪዎች

- ሙዚቃን ለመፃፍና ለማንበብ የሚያስችሉ መሠረታዊ ምልክቶችን ይለያሉ፣
- ሙዚቃን ለመፃፍና ለማንበብ የሚያስችሉ መሠረታዊ ክህሎት ይኖራቸዋል፣
- የሙዚቃን መሠረታዊ ንድፈ ሀሳብ ይረዳሉ፣
- የዲያቶኒክ እስኬልንና ባህላዊ የትዝታ ቅኝት አደራደርን ሕግን ያውቃሉ።

| *ዝርዝር ዓላማዎች* | *ይዘ ት* | *የመማር ማስተማር ዘዴዎች* |
|---|---|---|
| *ተማሪዎች ይህን ንዑስ ክፍለ ትምህርት ከተማሩ በኋላ፣*<br>• *መሠረታዊ የሙዚቃ ምልክቶችን ይገነዘባሉ፣*<br>• ከሙሉ ኖታ እሰከ ሩብ ኖታ ያሉ ኖታዎችን ከእነ እረፍት ምልክቶቻቸው በቅርጽና በጊዜ ቆይታ ይለያሉ፣<br>• የክልላቸውን ብሔራዊ መዝሙርና የዲሞክራሲ መርሆዎችንና እሴቶችን የሚያንፀባርቁ መዝሙሮችን ይዘምራሉ፣ | 2. *ንዑስ ክፍለ ትምህርት አንድ የኖታዎች የጊዜ ዋጋ (4 ክፍለ ጊዜ )*<br>2.1ሙሉ ኖታ፣ ግማሽ ኖታና ሩብ ኖታዎች ከእነ እረፍት ምልክቶቻቸው፣<br>2.2 መዝሙሮች(2 ክፍለ ጊዜ)<br>▪ መዝሙር የክልሉ ብሔራዊ መዝሙር<br>▪ መዝሙር የዲሞክራሲ መርሆዎችና እሴቶች የሚያንፀባርቁ መዝሙሮች፣ | • ኖታዎችና የእረፍት ምልክቶች ምን እንደሆኑና ጠቀሜታቸውን እንዲገልጹ ጥያቄ ማቅረብ፣<br>• ኖታዎችን ቅርጽና ንድፈ ሐሳብ በምሳሌዎች በዝርዝር ማሳየት፣<br>• የኖታዎችንና የእረፍት ምልክቶችን ዓይነትና ዋጋ ኖታዎችን የሚያሳይ ቻርት ወይም ኖታዎችን የያዙ ፍላሽ ካርዶችን በመጠቀም ተማሪዎቹ የበለጠ እንዲያውቋቸው ማድረግ።<br>• ኖታዎችንና የእረፍት ምልክቶችን ዓይነትና ዋጋ ተማሪዎች በተለያየ መንገድ (ጥቁር ሳሌዳ ላይ ወጥተው በመፃፍ፣ በወረቀት ላይ በመፃፍ ወዘተ...) እድል መስጠት፣ የክልላቸውን ብሔራዊ የሕዝብ መዘሙር እንዲዘምሩ ማድረግ፣<br>• የክልላቸውን መዝሙር በቡድን ሆነው ከተለማመዱ በኋላ በየቡድናቸው ለክፍሉ ተማሪዎች እንዲያቀርቡ ሁኔታዎችን በማመቻቸት መርዳት፣<br>• የዲሞክራሲ መርሆዎችንና እሴቶችን የሚያንፀባርቁ መዝሙር እንዲዘምሩ በየትምህርቱ ጣልቃ በማስገባት ተስማሚ የሆነውን መዝሙር የማስተማር ስልቶችን በመምረጥ ማለማመድና ማዘመር፣ |

| ዝርዝር ዓላማዎች | ይዘ ት | የመማር ማስተማር ዘዴዎች |
|---|---|---|
| • መዝሙሮቹ የሚያስተላልፉትን መልዕክት ያስረዳሉ፣ | | • ኖታዎች በመዝሙሮች ውስጥ የላቸውን ሚና ተማሪዎች/እንዲገነዘቡ ከመዝሙሩ ውስጥ ከኖሩዎችና የእረፍት ምልክቶች ጋር የተያያዙትን በማውጣት እንዲረዱ ማድረግ፣ |

**ክትትልና ግምገማ፡-**

- የሙዚቃ ምልክቶችንና የእረፍት መልክቶችን በዋጋቸውና በቅርጻቸው መለየታቸውን ማረጋገጥ፣
- የክልላቸውን መዝሙሮች መዘመራቸውን የሕዝብ መዝሙርና የዲሞክራሲ እሴቶችን የሚያንፀባርቁትን መዘሙሮችን በትክክል መዘመራቸውን ማረጋገጥ፣

**የማስማሪያ መሣሪያዎች፡-** ቴፕሬኮርደር ካሴቶች የሪትም ኖታ ቻርት፣ የኖታ ፍላሽ ካርድ፣ በቀላሉ የሚገኙ የሙዚቃ መሣሪያዎች

| ዝርዝር ዓላማዎች | ይዘ ት | የመማር ማስተማር ዘዴዎች |
|---|---|---|
| ተማሪዎች ይህን ንዑስ ክፍለ ትምህርት ከተማሩ በኋላ፡-<br>• የስታፍ ምንነትንና አጠቃቀምን ያስረዳሉ፣<br>• ጂ. ክሌፍን በሰታፍ ትክክለኛው ቦታ ላይ ይሠራሉ፣<br>• በጂ. ክሌፍ ስታፍ የመሥመሮችና የክፍት ቦታዎችን ስም ይለያሉ፣ | **ንዑስ ክፍለ ትምህርት ሁለት** (2 *ክፍለ ጊዜ* )<br><br>2.3 ሙዚቃን በስታፍ ላይ መጻፍ<br>• ስታፍ<br>• ጂ ክሌፍ<br>• በጂ ክሌፍ ስታፍ የኖታዎች አስያየም | • ተማሪዎች ስለሙዚቃ በስታፍ ላይ አፃፃፍ ያላቸውን ግንዛቤ በቅድሚያ እንዲናገሩ ማድረግ፣<br>• የስታፍ አሠራርን ሠቶ ማሳየት፣ ተማሪዎች እንዲሠሩት ማለማመድ፣<br>• የጂ. ክሌፍን አሠራርን በተለያዩ ዘዴዎች ማለማመድ፣<br>• የስታፍ የመሥመሮችን ክፍት ቦታዎች ስያሜ ማስተዋወቅ፣<br>• ተማሪዎች ከመምህሩ ያገኙትን የስታፍና የጂ. ክሌፍ አሠራርና አጠቃቀም በግልና በቡንድ በመሥራት በተሠራው ላይ እንዲወያዩ ማድረግ፣ |
| ይህን ንዑስ ክፍለ ትምህርት ተምረው ከአጠናቀቁ በኋላ፡-<br>• የጊዜ አመልካችና ተዛማጅ ምልክቶችን<br>• ይዘረዝራሉ፣ | **ንዑስ ክፍለ ትምህርት ሦስት** ( 2 *ክፍለ ጊዜ* )<br>የጊዜ አመልካች (Time signature) ምልክቶችና<br>• ቀላል የጊዜ አመልካች (Simple time | • እንደአመቺነቱ በሠሌዳ ላይ ወይም በቻርት ላይ በጂ. ክሌፍ ስታፍ የጊዜ አመልካች ምልክቶችን በመሥራት ተማሪዎች የአወቁዋቸውንና ያላወቁዋቸውን የሙዚቃ ምልክቶች እየለዩ |

| ዝርዝር ዓላማዎች | ይዘ ት | የመማር ማስተማር ዘዴዎች |
|---|---|---|
| • የምልክቶቹን አጠቃቀም ያስረዳሉ፣<br>• በምልክቶቹ በመጠቀም ኖታዎችን ይከፋፍላሉ፣ | signature) 2 3<br>• 4<br>• መደብ (Bar measure)<br>• መክፈያ መስመር (Bar line)<br>• መዝጊያ መሥመሮች (Double bar line) | እንዲናገሩ ማድረግ፣<br>• የተማሪዎች አቀራረብ መነሻ በማድረግ ስለጊዜ አመልካች ምልክቶች ምንነትና ጠቀሜታ ማብራሪያ መስጠት፣<br>• ስለአጠቃቀማቸውም በተከታታይ ምሳሌዎች ማስረዳት፣<br>• ተማሪዎች የተለያዩ ቀላል የጊዜ አመልካች ምልክቶችን ተጠቅመው ኖታዎችን በባር ላይን /መክፈያ መሥመር/ እንዲከፋፍሉ ማድረግ፣ |

## ክትትልና ግምገማ፡-

- ስለ ስታፍና ጂ. ክሌፍ ምንነት እንዲገልፁ ማድረግ
- በጂ. ክሌፍ ብቻ፣ የመሥመሮችና ክፍት ቦታዎችን ስም መለየታቸውን በጥያቄዎች ማረጋገጥ፣
- የጊዜ አመልካችና ተዛማጅ ምልክቶችን እንዲዘረዝሩ ማድረግ፣
- በጊዜ አመልካች መሠረት ኖታዎችን እንዲከፋፍሉ በማድረግ በምልከታ ማረጋገጥ፣

***ማስተማሪያ መሣሪያዎች፡-*** የስታፍ የክሌፍ ቻርት፣ የጊዜ አመልካች ቻርት፣

| *ዝርዝር ዓላማዎች* | *ይዘ ት* | *የመማር ማስተማር ዘዴዎች* |
|---|---|---|
| *ከዚህ ንዑስ ክፍለ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡-*<br>• *የዲያታቶኒክ ስኬል ምንነትን ያስረዳሉ፣*<br>• *ፔንታቶኒክ ስኬል ከዲያቶኒክ ስኬል እንዴት እንደሚገኝ ያሳያሉ፣*<br>• *በሙዚቃ ድምፆች መካከል የሚታዩ ርቀቶችን ይለያሉ፣*<br><br>• *ከግብርና ጋር የተያያዘ አንድ የእንግሊዝኛ መዝሙር ይዘምራሉ፣* | **ንዑስ ክፍለ ትምህርት አራት ( 8 ክፍለ ጊዜ)**<br>2.5 *የቦታዎች ርቀት /ኢንተረቫል/ ስኬሎች*<br>• *የሜጀር ስኬል አደራደር ሲ-ሜጀር*<br>• *ፔንታቶኒክ ስኬል(3 ክፍለ ጊዜ)*<br><br>2.6 *የባህላዊ ዜማ ድምፆች አደራደር - ትዝታ ቅኝት በመሥራት፣* / 2 *ክፍለ ጊዜ* /<br><br>2.7 *መዝሙር* /3 *ክፍለ ጊዜ*/<br>The Farmer in the dell. | • *ተማሪያዎች ስለዲያቶኒክና ፔንታቶኒክ ምንነት የሚያውቁትን እንንዲናገሩ ማድረግ፣*<br>• *ከተማሪዎች ሀሳብ በመነሳት ዲያቶኒክ ስኬል ሙሉ ቶንን እና ግማሽ ቶንን የአካተተ የሙዚቃ ድምፆች አደራደር ስልት እንደሆነ ማስረዳት፣*<br>• *የሙሉ ቶንና ግማሽ ቶን ልዩነትን ማስረዳት፣*<br><br>• *ዲያቶኒክ ስኬልን መሠረት በማድረግ ፔንታቶኒክ ስኬል እንዴት እንደሚገኝ ትዝታ ቅኝትን መነሻ በማድረግ የአደራደር ስልቱን ማሳየት፣*<br>• *ተማሪዎችን በቡድን በመከፋፈል እያንዳንዱ ቡድን በ"ጂ" ክሌፍ ስታፍ ላይ የ' ሲ' ሜጀር ስኬልንና የትዝታ ቅኝትን በመረጡት የኖታ ዓይነት /በሩብ ኖታ ወይም በግማሽ ኖታ/ በቻርት ላይ በማዘጋጀት የየቡድኑ መሪዎች ለክፍሉ ገለፃ እንዲሰጡ ማድረግ፣*<br>• *የመዝሙርን ቃላት ደጋግሞ በማስነበብ፣ እንደአመቺነቱ በተመረጠ የመዝሙር ማስተማር ዘዴ ተጠቅሞ መዘመሩን ማዘመር፣* |

## ክትትልና ግምገማ፡-

- *ዲያቶኒክ ስኬልንና ፔንታቶኒክ ስኬልን እንዲያብራሩ ጥያቄ ማቅረብ*
- *የዲያቶኒክ ስኬልና የፔንያቶኒክ ስኬል አደራደርን በ `ሲ' ሜጀር ስኬል ሠርተው እንዲያሳዩ በማድረግ በምልከታ ማረጋገጥ፣*
- *መዝሙሩን በቡድንና በግል በማዘመር በትክክል መዘመራቸውን ማረጋገጥ፣*

***የማስተማሪያ መሣሪያዎች፡-*** *ስኬሎችን የሚያሳዩ ቻርቶች በቀላሉ ሊገኙ የሚችሉ የሙዚቃ መሣሪያዎች በተለይ ዲያቶኒክ ስኬልና ፔንታቶኒክ ስኬልን ለመጫወት የሚያስችሉ ቢሆን ይመረጣል።*

## ክፍለ ትምህርት ሦስት ሰልፌጆ (Solfeggio) *(8 ክፍለ ጊዜ )*

*አጠቃላይ ዓላማዎች ተማሪዎች*

ከዚህ ክፍል ትምህርት በኋላ፡-

- *መሠረታዊ የሙዚቃ ኖታዎችን አነባብና አጠቃቀም ያውቃሉ፣*
- *ቀላል ምቶችን ስምቶ መጻፍና መልሰው መጫወት ይችላሉ፣*

| *ዝርዝር ዓላማዎች* | *ይዘ ት* | *የመማር ማስተማር ዘዴዎች* |
|---|---|---|
| *ተማሪዎች እነዚህን ንዑስ ክፍል ትምህርቶች ከተማሩ በኋላ፡-*<br>• ከሙሉ ኖታ እስከ ሩብ ኖታ ያሉትን ኖታዎች ያነባሉ፣<br>• የኖታዎችን ጠቀሜታ ይገልፃሉ፣<br>• ከሙሉ ኖታ እስከ ሩብ ኖታ ያሉ ቀላል ምቶችን ሰምተው ይጽፋሉ፣ | **3. ንዑስ ክፍለ ትምህርት አንድ**<br>የስልፌጆ ትርጉም፣ ጠቀሜታ<br><br>ከሙሉ ኖታ እስከ ሩብ ኖታዎች የንባብ ልምምድ /2 ክፍለ ጊዜ/<br><br>ከሙሉ ኖታ እስከ ሩብ ኖታዎች ያሉ ቀላል ምቶችን ስምቶ መጻፍና መጫወት /3 ክፍለ ጊዜ/ | • የስለፌጆን ትርጉምና ጠቀሜታን ማብራራት<br>• ከሙሉ ኖታ እስከ ሩብ ኖታዎች ያሉትን የኖታዎች ዋጋ እንዲዘረዝሩ ማድረግ፣<br>• ኖታዎች በዋጋቸው መሠረት እንዲያነቡ ገለፃ ማድረግ፣ ከሙሉ ኖታ እስከ ሩብ ያሉ የኖታዎችን አነባብ በተግባር ላይ በተመሠረተ እንቅስቃሴ ማሳየት፣<br>• ተማሪዎች ከመምህራቸው ያዩትን ትክክለኛ የኖታዎች አነባብ ስልት በግልና በቡድን ደጋግመው እንዲለማመዱ ማዱረግ፣ |
| • ሙሉ ኖታና ሩብ ኖታዎችን በመጠቀም ዶ፣ ሬ፣ሚ (Do, Re,mi) ድምፆችን ይዘምራሉ፣ | **ንዑስ ክፍለ ትምህርት ሁለት**<br>3.4 ከሙሉ ኖታ እስከ ሩብ በመጠቀም ዶ፣ ሬ፣ ሚ፣ (Do, ReError! Not a valid link. mi) የድምፅ ልምምድ / 3 ክፍለ ጊዜ / | • ከሙሉ ኖታ እስከ ሩብ ኖታዎች የተጻፉ ቀላል መልመጃዎችን በማዘጋጀት ስለአነባቡ መመሪያ መስጠትና ስህተት ካለ እንዲያርሙ ማገዝና ማበረታታት፣<br>• ምቶቹን በማሰማት ደጋግመው እንዲጽፉ ማለማመድ፣<br>• ከሰባቱ የሙዚቃ ሦስቱን ዶ፣ሬ፣ (Do, Remi) ድምፆች ላይ ትኩረት በማድረግ ወደ ላይና ወደ ታች በመውጣትና በማውረድ ከሙሉ ኖታ እስከ ሩብ ኖታ ካሉት ምቶች ጋር በቅደም ተከተለ በማቀናጀት ማዘመር፣<br>• በመጀመሪያ ትክክለኛውን ድምፅ መምህሩ በመዘመር ማስማት፣ በመቀጠል ተማሪ ዎች ከመምህራቸው የሰሙትን ድምፆች በግልና በቡድን እንዲሞክሩ ማድረግ ማበረታታት፣ |

## ክትትልና ግምገማ፡-

- ከሙሉ ኖታ እስከ ሩብ  ኖታ ያሉ ኖታዎችን ማንበባቸውን የተግባር  ጥያቄ በማቅረብ ማረጋገጥ፣
- ከሙሉ ኖታ  እስከ ሩብ  ኖታዎች በቃል ስምተው መጻፋቸውን በምልከታ ማረጋገጥ፣
- ኖታዎችን በመጠቀም ሦስት ድምፆችን መዘመር መቻላቸውን ጥያቄ ማቅረብ፣
- የዶ፣ሬ፣ሚ መዝሙር በግልና በቡድን  መ ዘመራቸውን በምልከታ ማረጋገጥ፣

**የማስማሪያ መሣሪያዎች፡-** ቴኘሬኮርደር በካሴት የተቀረፁ መዝሙሮች ቀሰሮ ሪትምስቲክ  ኪቦርድ  ዘይላፎን፣

## ክፍለ ትምህርት አራት ሙዚቃን ማድመጥ (*6 ክፍለ ጊዜ*)

***አጠቃላይ ዓላማዎች፡-****ተማሪዎች ይህንን ክፍለ ትምህርት ከተማሩ በኋላ፡-*

- *ሙዚቃን የማድመጥ ሥርዓቶችን ይረዳሉ፣*
- *ቀጭንና ወፍራም የሙዚቃ ድምፆችን ይለያሉ፣*
- *የተለያዩ የሙዚቃ መሣሪያዎችን ድምፅ ይለያሉ፣*

| *ዝርዝር ዓላማዎች* | *ይዘ ት* | *የመማር ማስተማር ዘዴዎች* |
|---|---|---|
| *ተማሪዎች ይህንን ንዑስ ክፍለ ትምህርት ከተማሩ በኋላ፡-*<br>• *ቀጭንና ወፍራም የሙዚቃ ድምፆችን ይለያሉ፣*<br>• *የአደማመጥ ሥርዓቶችን ይገነዘባሉ፣* | **4. ንዕስ ክፍለ ትምህርት አንድ/ 1 ክፍለ ጊዜ/**<br>1.4 *የአደማመጥ ሥርዓት፣*<br><br>4.2 *ቀጭንና ወፍራም የሙዚቃ ዱምፆችን መለየት፣* / 1 *ክፍለ ጊዜ* / | • *ተማሪዎች የማድመጥ ልምዳቸውን በቡድን ወይም በተናጠል ሆነው እንዲያካፍሉ ማድረግ፣*<br>• *ከማድመጥ ልምዳቸው ያገኙትን ጠቀሜታና ያጋጠማቸውን ችግር እንዲናገሩ ማድረግ፣*<br>• *የተማሪዎችን ተሞክሮ መሠረት በማድረግ ስለሙዚቃ የአደማመጥ ሥርዓት ማብራሪያ መስጠትና በሚያዳምጡበት ወቅት መከተል የሚገባቸውን ተግባራት መግለጽ፣*<br>• *ቀጭንና ወፍራም የሙዚቃ ድምፆችን መለየት እንዲችሉ ለዚህ የተመረጡ ሙዚቃ ማስደመጥና አስተያየታቸውን እንዲሰጡ ማድረግ፣* |
| • *የሙዚቃ መሣሪያዎችን ድምፅ ይለያሉ፣* | 4.3 *የሙዚቃ መሣሪያዎች ድምፅ መለየት፣* /1 *ክፍለ ጊዜ* / | • *በሙዚቃ መሣሪያዎች ብቻ የተቀነባበሩ ዜማዎችንና ዘፈኖችን በማስደመጥ ስለአዳመጡዋቸው የሙዚቃ መሣሪያዎች ዓይነት እንዲዘረዝሩ ማድረግ፣* |
| • *በሙዚቃ መሣሪያዎች የተቀነባበሩ በሕላዊና ዘመናዊ ዘፈኖችን ለይተው ይናገራሉ፣* | 4.4 *በተለያዩ የሙዚቃ መሣሪያዎች የተቀነባበሩ ባሕላዊ ዘፈኖችን ማዳመጥ፣* | • *በሙዚቃ መሣሪያዎች የተቀነባበሩ በሕላዊና ዘመናዊ ዘፈኖችን በቴፕ ማሰማት፣*<br>• *ስለአዳመጡት ባህላዊና ዘመናዊ ሙዚቃ የራሳቸውን አድናቆት እንዲገልጹ ማበረታታት፣*<br>• *የአዳመጡት ባህላዊ ዘፈኖችን ማን እንደተጫወታቸው በምን ዓይነት የሙዚቃ መሣሪያዎች እንደተቀነባበሩ በቡድን ከተወያዩ በኋላ የደረሱበትን ፍሬ ሐሳብ በየቡድናቸው ለክፍሉ ተማሪዎች እንዲገልጹና እንዲወያዩበት ማድረግ፣* |

## ክትትልና ግምገማ፡-

- ቀጭንና ወፍራም ድምፅ መለየታቸውን
- የተወሰኑ የሙዚቃ መሣሪያዎች ድምፅ መለየታቸውንና
- ባህላዊና ዘመናዊ ዘፈኖችን መለየታቸውን ጥያቄ በማቅረብ ማረጋገጥ፣

## የማስተማሪያ መሣሪያዎች፡-

- ቴፕሪኮደር፣ ካሴቶች፣ በሙዚቃ መሣሪያ የተቀነባበሩ ዘመናዊና ባህላዊ ዘፈኖች በካሴት የተቀረፁ፣
- በሙዚቃ መሣሪያ ብቻ የተቀነባበሩ ካሴቶች ወዘተ…

## ክፍል ትምህርት 5 የሙዚቃ ታሪክ *(8 ክፍለ ጊዜ)*

***አጠቃላይ ዓላማ፡-*** ተማሪዎች ይህን ክፍል ትምህርት ከአጠናቀቁ በኋላ

- የክልላቸውን የሙዚቃ ታሪክ ያውቃሉ፣
- ለዘመናዊ ሙዚቃ እድገት ት/ቤቶች የነበራቸውንና ወደፊት የሚኖራቸውን ሚና ይገነዘባሉ፣

| *ዝርዝር ዓላማዎች* | *ይዘ ት* | *የመማር ማስተማር ዘዴዎች* |
|---|---|---|
| *ተማሪዎች ይህን ንዑስ ክፍለ ትምህርት ከተማሩ በኋላ*<br>• የክልላቸውን የሙዚቃ ታሪክ ይናገራሉ፣<br>• የክልላቸውን ታዋቂ የባህላዊ ሙዚቃ ባለሙያዎችን ታሪክና ሥራዎችን ያብራራሉ፣ | **5. ንዑስ ክፍለ ትምህርት አንድ** ( *2 ክፍለ ጊዜ)*<br>5.1 የክልሉ ሙዚቃ ታሪክ፣<br>▪ ከባህላዊ ሙዚቃ አንፃር፣<br>▪ ከዘመናዊ ሙዚቃ አንፃር፣<br>5.2 የክልሉ ታዋቂ የባህላዊ ሙዚቃ ባለሙያዎችን ታሪክና ሥራዎች በድምፃዊነት፣ በመሣሪያ ተጫዋችነት በተወዛዋዥነት /ቢያንስ ባለሙያ/ /1 ክፍለ ጊዜ / | **የመማር ማስተማር ዘዴዎች**<br>• ተማሪዎችን በቡድን በመከፋፈል ስለክልላቸው የሙዚቃ ታሪክ አንጋፋዎችን ጠይቀው መረጃዎችን እንዲያሰባስቡ ማድረግ፣<br>• እያንዳንዱ ቡድን ያሰባሰበውን ታሪክ በጽሑፍ አዘጋጅቶ በየተራ ለውይይት እንዲያቀርቡ ማድረግ፣<br>• ቡድኖቹ በአቀራረባቸው የሚመሳሰሉበትን የሚለያዩበት በዝርዝር መያዝ፣<br>• ከክልሉ ባህል ቢሮ፣ ከአስተዳደር ወዘተ… ለጉዳዩ ቅርበት ያላቸውን ግለሰቦች በመጋበዝ ያላቸውን ልምድ እንዲያካፍሉ ማድረግ፣<br>• ተማሪዎች በእነዚህ እንግዶች የቀረበውን በስፖርት መልክ እንዲዘግቡ ማድረግ፣ |
| ይህንን ንዑስ ክፍለ ትምህርት ሲያጠናቅቁ<br>▪ የኢትዮጵያ ትምህርት ቤቶች ለዘመናዊ ሙዚቃ ባንድ መጠናከር የነበራቸውን ሚና ያስረዳሉ፣<br>▪ የዘመናዊ ሙዚቃ ባንድ በት/ቤቶች የነበራቸውን ሚናና አስተዋፅኦ ይዘረዝራሉ፣ | **ንዑስ ክፍለ ትምህርት ሁለት**<br>5.3 የሀገር አቀፍ ሙዚቃ ታሪክ /1934-1966/<br>5.2 መዝሙር፣ የክልሉን ውበትና ልማትን የሚያንፀባርቁ /ሁለት መዝሙር/ 2 ክፍለ ጊዜ/ | ▪ በሀገር አቀፍ ደረጃ ት/ቤቶች ለሙዚቃ እድገት ያበረከቱትን አስተዋፅ በትረካ መልክ ማቅረብ፣<br>▪ ተማሪዎች በጋራ ውይይት እንዲያዳብሩ ማበረታታት፣<br>▪ አመቺ የመዝሙር ማስተማሪያ ዘዴዎች በመጠቀም መዝሙሩን /መዝሙሮችን/ ማስጠናት፣ |

***ክትትልና ግምገማ፡-***

- *የቡድን ሥራዎች  መከናወናቸውን ማረጋገጥ፣*
- *እያንዳንዱ ተማሪ ስለቡድን ሥራው ማብራሪያ እንዲሰጥ በማድረግ ማረጋገጥ፣*
- *ተማሪዎች የአደመጡትን ታሪክ በራሳቸው አቀራረብ እንዲናገሩ በማድረግ ማረጋገጥ፣*

***የማስተማሪያ መሣሪያዎች፡-*** *ቴፕሪኮርደር፣ ካሴቶች ፎቶግራፎች፣*

- *ከክልሉ ውበትና ልማት ጋር የተያያዙ መዝሙሮችን ይዘምራሉ፣*
- *በመዝሙሩ /መዝሙሮች/ ውስጥ የተቀመጡ ፅንሰ ሀሳቦችንን ይገነዘባሉ፣*

**ክፍለ ትምህርት ስድስት ባህላዊ ሙዚቃ /18 ክፍለ ጊዜ/**

አጠቃላይ ዓላማዎች፡- ተማሪዎች ይህንን ክፍለ ትምህርት ተምረው ከጠናቀቁ በኋላ

- አካባቢያቸው የሚገኙትን ባህላዊ ሙዚቃዎችና ዳንኪራዎችን ይረዳሉ፣
- ባህላዊ ሙዚቃዎችንና ዳንኪራዎችን መሰብሰብና መጫወት ይችላሉ፣

| ዝርዝር ዓላማዎች | ይዘ ት | የመማር ማስተማር ዘዴዎች |
|---|---|---|
| | **6. ንዑስ ክፍለ ትምህርት አንድ ፡- ባህላዊ ሙዚቃዎች አሰባሰብና አጨዋወት** | |
| ተማሪዎች ይህንን ንዑስ ክፍለ ትምህርት ከተማሩ በኋላ፡-<br>▪ ከሥራ፣ ከእርሻና ከአርብቶ አደር ሥራ ጋር የተያያዙ ባህላዊ ዘፈኖችንና/ሙዚቃዎችን ይተነትናሉ፣<br>▪ ከሕብረት መልካም ሥነ ምግባርና ከበዓላት ሥነ ሥርዓቶች /ድርጊቶች/ ጋር የተያያዙ ባህላዊ ዘፈኖች ከእነ አልባሳቱ በመሰብሰብ ይተነትናሉ፣ | 6.1 ከሥራ፣ ከእርሻና ከአርብቶ አደር ሥራ ጋር የተያያዙ ባህላዊ ዘፈኖች ዳንኪራዎችና /ሙዚቃዎች/ ግጥምና ዜማ እንዲሁም እነዚህን የሚያጅቡ የሙዚቃ መሣሪያዎችን መሰብሰብና መተንተን /5 ክፍለ ጊዜ/<br>6.2 ከሕብረት፣ ከመልካም ሥነ ምግባርና ከበዓላት ሥነ ሥርዓቶች ጋር የተያያዙ ዘፈኖችና አልባሳቱ መሰብሰብና መተናን /5 ክፍል ጊዜ/ | ▪ ተማሪዎች ስለ ባህላዊ ሙዚቃ ከራሳቸው ልምድ የሚያውቁትን እንዲናገሩ ማበረታታት፣<br>▪ በባህላዊ ሙዚቃዎችና ዳንኪራዎች አሰባሰብና አጨዋወት አላማና የማከናወኑ ዋና ዋና ተግባራትን በሚገባ እንዲረዱ ማድረግ፣<br>▪ ተማሪዎች ከራሳቸው ልምድና ተሞክሮ ስለ ባህላዊ የሥራ፣ የእርሻና የአርብቶ አደር ባህላዊ ዘፈኖች፣ ዳንኪራዎችና /ሙዚቃዎች/ አይነቶችና ጠቀሜታ እንዲወያዩበት ማድረግ፣<br>▪ የዘፈኖቹን አተናተን መስፈርቶች በጋራ መንደፍ፣ /ትንተናው የሚያተኩርባቸው ግጥምና ዜማ፣ የሚያጅቡ የሙዚቃ መሣሪያዎች ዓይነት ከተቻለ የአልባሳቱ ዓይነት፣ አጨዋወት፣ ጨዋታው የሚከናወንበት ጊዜና ቦታ ወዘተ.. ላይ የሚያተኩር መሆኑን እንዲረዱ ማድረግ፣/<br>▪ ዘፈኖቹን በመስፈርቱ መሠረት እንዴት እንደሚሰበሰቡና እንደሚተነተኑ ማስረዳት፣<br>▪ የአሰባሰብ ዘዴው ላይ ምን እንደሚጠየቅ፣ ማን እንደሚጠየቅ የተጠየቀው እንዴት እንደሚቀነባበር ወዘተ... ተወያይቶ በጋራ ስምምነት ላየ መድረስ፣ |

| ዝርዝር ዓላማዎች | ይዘ ት | የመማር ማስተማር ዘዴዎች |
|---|---|---|
| | | ▪ የሚቻል ከሆነ የሚበሰበሱ ዘፈኖች በቴፕ እንዲቀርጹዋቸው ማድረግ፣ የአቀዳድ ዘዴውን የማይክሮፎን አያያዝ የቴፕ አቀራረጽ ዘዴዎችን ማሳየት በቡድን ተከፋፍሎ መረጃዎችን<br>▪ መደረጃዎቹን በቡድን ተከፋፍለው እንዲሰበስቡና እንዲተነትኑ ማድረግ፣ መሰብሰብና መተንተን፣<br>▪ የተተነተነውነ የቡድን ሥራ ከፍሉ ተማሪዎች ተራ በተራ ማቅረብ፣<br>▪ የክፍሉ ተማሪዎች በቀረበው ላይ አስተያየት እንዲሰጡበት ማድረግ፣<br>▪ ዘፈኖቹን በመስፈርቱ መሠረት እንዴት እንደሚሰበሰቡና እንደሚተነትኑ ማስረዳት<br>▪ በሥራውመ ሂደት ምን ችግር እንዳጋጠማቸውና እንዴት ችግሩን እንደፈቱ ሪፖርት ለተማሪዎች እንዲያቀርቡ ማድረግ፣ |

ክትትልና ግምገማ፡-

- የሰበሰቡትን ባህላዊ ሙዚቃዎች ዘፈኖችን በምልከታ ማረጋገጥ
- የትንተናውን ዘገባ መገምገም

የማስተማሪያ መሣሪያዎች፡-

- ቴፕርኮርደር
- ካሴት

| ዝርዝር ዓላማዎች | ይዘ ት | የመማር ማስተማር ዘዴዎች |
|---|---|---|
| ንዑስ ክፍለ ትምህርት ሁለት | | |
| ተማሪዎች ይህንን ንዑስ ክፍለ ትምርት ካጠናቀቁ | ባህላዊ ሙዚቃዎችና ዳንኪራዎችን ከሙዚቃ | ▪ ተማሪዎች ካሁን በፊት ባህላዊ ሙዚቃዎችና |

| ዝርዝር ዓላማዎች | ይዘ ት | የመማር ማስተማር ዘዴዎች |
|---|---|---|
| በኋላ<br><br>▪ ከሥራ፣ ከእርሻና ከአርብቶ አደር ጋር የተያያዙ ዘፈኖችንና ዳንኪራዎችን ይጫወታሉ፣<br>▪ ከዘፈኖቹ ጋር በአካባቢያቸው የተለመዱ ቀላል የምት ሙዚቃ መሣሪያዎችን አቀናጅተው ይጫወታሉ፣<br>▪ በዘፈኖቹና ዳንኪራዎቹ ጨዋታ ይደሰታሉ፣<br>▪ ከሕብረት፣ ከመልካም ሥነ ምግባርና ከበዓላት ጋር የተያያዙ ባህላዊ ዘፈኖችንና ዳንኪራዎችን ይጫወታሉ፣<br><br>▪ ከዘፈኖቹ ጋር በአካባቢያቸው የተለመዱ ቀላል የሙዚቃ መሣሪያዎችን አቀናጅተው ይጫወታሉ<br>▪ በጨዋታዎቹ ይደሰታሉ። | መሣሪያዎች ጋር በማቀናጀት መጫወት፣<br><br>6.3 ከሥራ ከእርሻ ከአርብቶ አደር ጋር የተያያዙ ባህላዊ ዘፈኖችንና ዳንኪራዎችን መጫወት / 5 ክፍለ ጊዜ/<br><br>6.4 ከሕብረት፣ ከመልካም ሥነ ምግባርና ከበዓላት ጋር የተያያዙ ባህላዊ ዘፈኖችንና ዳንኪራዎችን መጫወት፣ / 3 ክፍለ ጊዜ/ | ዳንኪራዎችን ተጫውተው ያውቁ እንደሆነ ልምዳቸውን ለክፍሉ ተማሪዎች እንዲያካፍሉ በማድረግ ማበረታታት፣<br>▪ የባህላዊ ሙዚቃዎችና ዳንኪራዎችን የአጨዋወት ስልትና ቅደም ተከተልን እንደዚሁም ከሙዚቃ መሣሪያዎች ጋር እንዴት በማቀናጀት መጫወት እንደሚቻል ማብራሪያ መስጠት፣<br>▪ ተማሪዎችን በቡድን መመደብና የአሠራር ቅደም ተከተልን አውጥተው ባህላዊ ዘፈኖችንና ዳንኪራዎችን እንዲለማመዱ ማድረግ፣<br>▪ የሙዚቃ መሣሪያዎችን መጫወት የሚችሉ ተማሪዎችን መለየትና እነዚህ ተማሪዎች አጨዋወቱን ለክፍሉ ተማሪዎች እንዲያሳዩ ማድረግ፣<br>▪ ስለ ሙዚቃ መሣሪያዎች አጨዋወት ተማሪዎች ምንም ልምድ ከሌላቸው ከተቻለ በአካባቢው መሣሪያዎችን የሚጫወቱ ሰዎችን መጋበዝና እንዲያሳዩዋቸው ማድረግ፣<br>▪ ተማሪዎችን በቡድን በመመደብ የመረጡትን ባህላዊ ሙዚቃዎችና ዳንኪራዎች እንዲለማመዱ ማድረግ የሙዚቃ መሣሪያዎችን የማጫወቱትን ተማሪዎች በየቡድኑ አሰባጥሮ መመደብና ስለ ልምምዱ እያንዳንዱ ቡድን የራሱን ፕሮግራም እንዲቀይስ ማድረግ፣ |

| ዝርዝር ዓላማዎች | ይዘ ት | የመማር ማስተማር ዘዴዎች |
|---|---|---|
| | | ▪ የልምምድ ጊዜያቸውን ሲያጠናቅቁ እያንዳንዱ ቡድን ተራ በተራ ለክፍሉ ተማሪዎች እንዲያቀርብ ማድረግ፣<br>▪ በቀረበው ዝግጅት ላይ የክፍሉ ተማሪዎች አስተያያታቸውን እንዲሰጡ በማድረግ አንዱ ከሌላው እንዲማር ማድረግ፣ |

**ክትትልና ግምገማ፡-**

- ከሥራ ከእርሻና ከአርብቶ አደር ጋር የተያያዙ ዘፈኖችና ዳንኪራዎችን መጫወታቸውን በምልከታ ማረጋገጥ፣
- ዘፈኖቹን ከአካባቢው የሙዚቃ መሣሪያዎች ጋር በማቀናጀት መጫወታቸውን ማየት፣
- ዘፈኖቹ ያሳደሩባቸውን ስሜቶች እንዲገልፁ በማድረግ ማረጋገጥ፣

**የማስማሪያ መሣሪያዎች፡-** ቴፕሪኮርደር፣ ካሴት፣ የተለያዩ በአካባቢ የተለመዱ የሙዚቃ መሣሪያዎች ከላይ ከተጠቀሱት ብህላዊ ዘፈን ዓይነቶች ጋር የሚሄዱ አልባሳት፣

**ክፍለ ትምህርት ሰባት የሙዚቃ መሣሪያዎች/ 6 ክፍለ ጊዜያት/**

አጠቃላይ ዓላማ፡- ተማሪዎች ይህን ክፍለ ትምህርት ካጠናቀቁ በኋላ

- የክልሉንና የሀገረ አቀፍ የምት ሙዚቃ መሣሪያዎች ዓይነት አሠራርና አጠቃቀምን ያውቃሉ፣

| ዝርዝር ዓላማዎች | ይዘ ት | የመማር ማስተማር ዘዴዎች |
|---|---|---|

| ዝርዝር ዓላማዎች | ይዘ ት | የመማር ማስተማር ዘዴዎች |
|---|---|---|
| **7. ንዑስ ክፍለ ትምህርት አንድ / 1 ክፍለ ጊዜ /** | | |
| ይህን ንዑስ ክፍለ ትምርት ካጠናቀቁ በኋላ ተማሪዎች<br>▪ የክልሉን የምት ሙዚቃ መሣሪያ ዓይነቶችን ይዘረዝራሉ፣<br>▪ የክልሉን የምት ሙዚቃ መሣሪያዎች ከአካባቢው ከሚገኙ ቁሳቁሶች ሠርተው ያሳያሉ፣<br>▪ የክልሉን የምት ሙዚቃ መሣሪያዎችን አጠቃቀም ያስረዳሉ<br>▪ ስለ ተፈጥሮ ሀብት የደንና ዱር አራዊት ጥበቃና እንክብካቤ የሚያንፀባርቁ መዝሙሮችን ይዘምራሉ፣<br>▪ መዝሙሩ የሚያስተላልፈውን መልእክት ያስረዳሉ፣ | 7.1 የክልሉ የምት ሙዚቃ መሣሪያዎች<br>▪ በእጅ መዳፍ የሚመቱ<br>▪ በማጋጨትና በማነቃነቅ የሚሠሩ<br>▪ የሚሠሩባቸው ጥሬ ዕቃዎችና አሠራር<br>▪ በሥራ ላይ የሚውሉበት ወቅት<br><br>7.2 መዝሙር /2 ክፍለ ጊዜ/<br>▪ የደንና ዱር አራዊት እንክብካቤና ጥበቃን የሚያንፀባርቅ መዝሙር/መዝሙሮች/፣ | ▪ ተማሪዎች ከራሳቸው ተመክሮ ተነስተው ስለክልሉ የምት መሣሪያዎች የሚያውቁትን ለክፍል ጓደኞቻቸው እንዲዘረዝሩ ማድረግ፣<br>▪ ከተማሪዎች የቀረቡትን አስተያየቶች መነሻ በማድረግ ስለ ክልሉ የምት ሙዚቃ መሣሪያዎች ማብራራት፣<br>▪ ተማሪዎችን ቡድን በማደራጀት የክልሉ የምት ሙዚቃ መሣሪያዎች የሚሠሩበት ጥሬ ዕቃዎች ከምን እንደሚሰሩ እንዲወያዩ ማድረግ፣<br>▪ የተማሪዎች ቡድኖች የአቀረቡትን የጥሬ ዕቃዎች በተጠሪያቻው በኩል ለክልል ጓደኞቻቸው እንዲያቀርቡ ማድረግ፣<br>ለእያንዳንዱ ቡድን መሣሪያዎችን በመመደብ በድኑ የተመደበለት መሣሪያ የተሠራበት ጥሬ እቃዎች በማሰባሰብ መሣሪያዎቹን እንዲሠሩ ማድረግ፣<br><br>▪ ቡድኖቹ ስለአዘጋጁዋቸው መሣሪያዎች አሠራርና ለክፍሉ ተማሪዎች በየተራ ገለፃ እንዲሰጡ ማድረግ፣<br>▪ በተማሪዎች በተዘጋጁ መሣሪያዎች አጨዋወቱን በቡድን ማለማመድ፣<br>▪ እንደአመቺነቱ የምት መሣሪያዎችን ተጫዋች ባለሙያዎችን በመጋበዝ ለአሰራራቸው፣ አጨዋወታቸው ገለፃ እንዲሰጡ ማዳረግ፣<br>▪ እንደአመቺነቱ በተለያዩ የመዝሙር ማስተማር ዘዴዎች |

| ዝርዝር ዓላማዎች | ይዘ ት | የመማር ማስተማር ዘዴዎች |
|---|---|---|
| | | በመጠቀም ማዘመር፣ |

ክትትልና ግምገማ፡-

- የክልሉን የምት ሙዚቃ መሣሪያዎች በስም እንዲዘረዝሩ  በጥያቄ ማረጋገጥ
- እያንዳንዱ ቡድን የአዘጋጀውን የምት ሙዚቃ መሣሪያዎችን ትክክለኛነት በምልከታ ማረጋገጥ፣
- የመሣሪያዎቹን አጠቃቀም በምልከታ ማረጋገጥ፣
- መዝሙሩን በትክክል መዘመራቸውን ማረጋገጥ፣
- ስለተፈጥሮ ሀብት ጥበቃ እንክስካቤ ያገኙትን ዕውቀት ጥያቄ በማቅረብ ማረጋገጥ፣

- የማስተማሪያ መሣሪያዎች፡-  በክልሉ በሥራ ላይ የዋሉ የምት መሣሪያዎች፣ /በአካል በሥዕል፣ በፎቶግራፍ ወዘተ…/

| ዝርዝር ዓላማዎች | ይዘ ት | የመማር ማስተማር ዘዴዎች |
|---|---|---|
| **ንዑስ ክፍለ ትምህርት ሁለት / 2 ክፍለ ጊዜ /** | | |
| ይህን  ንዑስ ክፍለ ትምህርት ተምረው ሲጨርሱ ተማሪዎች<br>▪ ሀገር አቀፍ የምት ሙዚቃ መሣሪያዎችን በስም ይዘረዝራሉ፣<br>▪ ሀገር አቀፍ የምት ሙዚቃ መሣሪያዎችን | 7.3 ሀገር አቀፍ የምት ሙዚቃ መሣሪያዎች ዓይነት አሠራር<br>▪ የአጨዋወት ስልት /በእጅ መዳፍ የሚመቱ፣ በማጋጨትና በማነቃነቅ የሚሠራባቸው/ | ▪ በቅድሚያ ተማሪዎች ስለ ሀገር አቀፍ የምት ሙዚቃ መሣሪያዎች የሚያውቁትን እንዲናገሩ ማድረግ፣<br>▪ ተማሪዎች ከተናገሩት በመነሳት ስለ ዋና ዋና ሀገር አቀፍ የምት ሙዚቃ መሣሪያዎች |

| ዝርዝር ዓላማዎች | ይዘ ት | የመማር ማስተማር ዘዴዎች |
|---|---|---|
| አሠራር ያስረዳሉ፣<br>▪ ሀገር አቀፍ የምት ሙዚቃ መሣሪያዎችን አጫዋወት ያሳያሉ፣<br><br>▪ መሣሪያዎቹ በሥራ ላይ የሚውሉባቸውን ጊዜያት /ወቅቶች/ ይናገራሉ፣<br>▪ ስለ ቤተሰብ ምጣኔ ምንነት ያብራራሉ፣ | ▪ የሚሩባቸው ጥሬ ዕቃዎች<br>▪ በሥራ ላይ የሚውሉበት ጊዜያት /ወቅቶች/1 ክፍለ ጊዜ/<br><br>7.4 መዝሙር /አንድ መዝሙር/<br>ስለቤተሰብ ምጣኔ አስፈላጊኔት የሚያንፀባርቅ / 2 ክፍለ ጊዜ / | አይነትና አሠራር ማብራራት፣<br>▪ እንደአመቺነቱ ተማሪዎችን በቡድን በማደራጀት ለእያንዳንዱ ቡድን አንደንድ የምት መሣሪያዎችን በመመደብ ስለአሠራራቸውና አጠቃቀማቸው በሥራ ላይ ስለሰሩበት ጊዜያት በቃለ መጠይቅ ወይም መፅሐፍ በማንበብ ወዘተ.. መረጃዎችን እንዲያሰባስቡ ማድረግ፣<br>▪ ቡድኖች በአሰባሰቡት መረጃዎች ላይ ውይይት ማካሄድ<br>▪ በተለያዩ የመዝሙር ማስተማር ዘዴዎች በመጠቀም መዝሙርን ማዘመር፣ |

**ክትትልና ግምገማ፡-**

- ሀገር አቀፍ የሙዚቃ መሣሪያዎችን በስም መለየታቸውን በጥያቄ ማረጋገጥ፣
- ስለመሣሪያዎቹ አሠራር እንዲገልፁ ማድረግ፣
- የቡድን ሥራዎችን ማከናወናቸውን በምልከታ ማረጋገጥ፣
- የመዝሙሩን ጠቀሜታ እንዲያስረዱና ስለቤተሰብ ምጣኔ ምንነት ማብራሪያ እንዲሰጡ ጥያቄ ማቅረብ

**የማስተማሪያ መሣሪያዎች፡-** የሀገር አቀፍ የሙዚቃ መሣሪያዎች ዓይነት /በአካል በሥዕል በፎቶግራፍ/